# <u>ከመጠምጠም መማር ይቅደም</u>

*<u>ሃገርና ሕዝብ የሚድነው በሰከነ አዕምሮ ማሰብ ሲቻል ብቻ ነው</u>*

**ከለማ በገበያ**

ለዚህ ጽሁፌ መነሻ ምክንያት የሆነኝ ታደለ ግርማ በደብተራው ድረ-ገጽ ላይ " የወሬን ቀርፋዳ ዋንጫ ቅቤ አያርሰውም " ( ከወያኔ ጋር ዛሬም እርቅ ይታሰባል? ) በሚል ርዕስ ያቀረቡት ሂሳዊ ጽሁፍ ነው። ሜይ 5 2007 በአሲምባ ፓልቶክ ስለተላለፈውና ኦታዋ ካናዳ ስለተከናወነው ሕዝባዊ ስብሰባ ( በሂስ አቅራቢው አጠራር <u>የምሁራን ስብሰባ</u> ) የግል ግንዛቤንና ትዝብትን ሳይደብቁ በሂስ መልክ መግለጹ ተገቢና ወደፊት ታግለን ልንገነባው በምናቅደው ስርዓት የበለጠ ዕውን እንዲሆን የምንደክምበት የጋራ ጉዳያችን በመሆኑ ሊበረታታ የሚገባው ነው። በቅድሚያ ባገራችን "ታደለ" ( ያውም ታደለ ግርማ ) የወንድ ልጅ ያደባባይ ስሙ ነውና አቶ ታደለ እያልኩ እንድጠራዎ ይፍቀዱልኝ።

የሂስ ጥበብ አባት ነው የሚባለው አርስቶትል <u>ፖዬቲክስ</u> በተሰኘው ስራው ውስጥ ሂስ ስለመስጠትና መቀበል የሚከተሉትን ሁለት መሰረታዊ ነጥቦች መሰንዘሩን ያውቁ ይሆን? ታላቁ ፈላስፋ አርስቶትል ስለሂስ ሲገልጽ፦

1ኛ. ሂስ ለመስጠት የሚፈቅድ ማንኛውም ግለሰብ የሚሰጠው ሂስ ዓላማው ምን እንደሆነ አስቀድሞ ማወቅ ቀዳሚ ተግባሩ መሆን ይገባዋል። እንዲሁም፦

2ኛ. ሂሱ ለማንና እንዴት ነው የሚሰጠው ብሎም በብርቱ ሊያስብበት ይገባል- ይለናል።

<u>ውድ አቶ ታደለ!</u>

ለጽሁፍዎ ርዕስ "የወሬን ቀርፋዳ ዋንጫ ቅቤ አያርሰውም" የሚል ርዕስ መስጠትዎ መብትዎ ቢሆንም፤ የወሬ ቀርፋዳ ያሉት የእርቅን ጉዳይ ይሆን? ለመሆኑ በግንቦቱ ምርጫ የተሳተፉት ሁለቱም ተቃዋሚ ድርጅቶች ኢዴሃህና ቅንጅት ሕወሃት/ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን ሕዝብ ድምጽ ባደባባይ ከሰረቀ በሁዋላ እንኳ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ( ገዢውን ፓርቲ ሳይቀር ) ያሳተፈ ብሔራዊ ጉባዔ እንዲጠራ ሲወተውቱ አልነበረምን? ዛሬም ድረስ እኮ ይህን ጥሪያቸውን አላቆሙም። ከወያኔ ጋር ድርድር በማድረግና ለወያኔ በማደር መካከል የገደል ያሕል ልዩነት እኮ ነው ያለው። በድርድሩ ሂደት ተሳትፈውም ሆነ ከተቃዋሚው ወገን ነን እያሉ ሲምሉ ሲገዘቱ የነበሩ ከመቅጽበት የናቴ መቀነት ጠለፈኝ የሚል ምክንያት በመደርደር ከወያኔ ፓርላማ የተሸጎጡ መኖራቸው ከዚህ ድርጊት የታቀቡትን ሁሉ በጥርጣሬና ባይነ ቁራኛ እንዲጠበቁ አድርጓቸው ይሆን? በዚህ ዓይነትማ የማይተማመን ባልንጀራ እየሆነ ለሃገራችንም ለሕዝቧም ሳንፈይድ አንዳችን አንዳችንን ስንጠብቅ በርስ በርስ እረኝነት ስንዳክር ልንኖር እኮ ነው። ለመሆኑ ከግንቦቱ ምርጫ ቀደም ባሉት ጥቂት ወራት ኢዴሃህ (ኢሕአፓ በአባልነት የሚገኝበት) ለምርጫው ዴሞክራሲያዊ መሆን ይበጅ ዘንድ ካቀረባቸው የድርድር ነጥቦች በጣም ጥቂቶቹ ተቀባይነት ማግኘታቸውን ማስታወስ ያስፈልግ ይሆን? እርግጥ ነው ድርድሮቹ መሰረታዊ ለውጥ አስገኝተዋልን? ሲባል ምላሹ አላስገኙም ነው። ካላስገኙ ሕዝብ የስልጣን ባለቤት የሚሆንበትን ዘዴ ከሕዝቡ ጎን በመሆን በጋራና በሰከነ ውይይት መቀየስ እንጂ እርቅን፣ ድርድርን፣ የጠረጴዛ ዙሪያ ውይይትን የመረጠ ወይም የዚህን የትግል ስልት ጠቀሜታ ያነሳ ብሎም ስለዚህ ያሰበ ሁሉ ውጉዝ ከመአርዮስ ነው ለማለት መከጀል ትክክል ካለመሆኑም በላይ የኢትዮጵያን ሕዝብ የትግል ታሪክ ውጣ ውረድ ከቁብ ያላስገባ ትንታኔ ለመስጠት እንደመከጀል ይቆጠራል።

ውድ አቶ ታደለ!

በጽሁፍዎ ንዑስ ርዕስ “ከወያኔ ጋር ዛሬም እርቅ ይታሰባል?” ሲሉ ጠይቀዋል። ወረድ ሲል ባቀረቡት የግል አስተያየትዎ የማይታሰብ ስለመሆኑም ነግረውናል። ለመሆኑ በመርህ ደረጃ ደም ፈሶ አጥንት ተከስክሶ በመግደል በማሰር በጠመንጃ ተገኘ ከሚባል ( የወያኔውን ዓይነት ) “ሰላም” በጠረጴዛ ዙሪያ በሰከነ ውይይት የሚገኝ ከሆነ መሞከሩ ምኑ ላይ ነው ክፋቱ? እንኳን ሊሞከር አይታሰብም ለማለት መቃጣትዎ እጅግ ያስገረመው የደቡብ አፍሪካን ታሪክ ከጠቀሱልን በሁዋላ ነው (ከአክብሮት ጋር የደቡብ አፍሪካን ታሪክ መልሰው ይመረምሩ ዘንድ እጠይቀታለሁ) ። የደቡብ አፍሪካው ዘረኛ የቦታ ስርዓት እኮ በአሸባሪነት ከፈረጀውና በሚሊዮን የሚቆጠሩ አባላትንና ደጋፊዎቹን ከረሸነበት ከኤንሲ መሪዎች ጋር ለድርድር ለመቀመጥ ተገዷል- ከነጻነት በፊት በተደረጉ ግፊቶች። እቅጩን እንነጋገር ከተባለ እኮ ማንዴላን የመሰለ አስተዋይ የተወለደው በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ደቡብ አፍሪካውያን አጥንትና ደም ከተከሰከሰበት ማሕጸን ውስጥ ነው። በሰላማዊና ድርድር በሚካሄድበት ትግል ውስጥም ስቃይ መከራና ሞት አይቀሬ ናቸው- ክቡር ስቃይ ክቡር መከራ ክቡር ሞት መሞትን የመሰለ ( እንደትናንቶቹ የኢሕአፓ ጀግኖች ) ታላቅ ጸጋ አይገኝም እንጂ። እናም እርቅ ስለተባለ አልጋ ባልጋ ነው መንገዱ ማለት እንዳይደለ ልብ ሊባል ይገባል። ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ለረጅም ጊዜ በተለይ ተቃዋሚ በሚባለው ወገን ተገቢውን ግንዛቤ ያላገኘ እከሌ\እከሊት ይህን አለ\አለች ወይም ይህ ድርጅት በዚህ ስልት ልጠቀም አለ እየተባለ የህዝብ ወገን የሆኑትን እርስ በርስ ሲያሻኩት የኖረ ጎጂ አስተሳሰብ ነበር- በቅርቡ ነው ሁሉን አቀፍ በሆነ ዘዴ ጠላትን መዋጋት አስፈላጊ መሆኑ ግንዛቤ ያገኘ። ያውም በነኢሕአፓ ግፊት። ለማንኛውም በሰላማዊም ሆነ በትጥቅ የተሞከሩት ሕዝባዊ የትግል ሂደቶች በሞት የታጀቡ አልነበሩም ብሎ አይኔን ግንባር ያርገው ካልተባለ በስተቀር ሁሉም ክቡሩን የሕይወት መስዋዕትነት ሳይቀር የሚያስከፍሉ ናቸው።

በነገራችን ላይ የእርቅ አማራጭ ለምን ሰምተን ከሚሉ ሌሎችም ጉዳዩ ትጥቅ አስፈቺ ነው የሚል መከራከሪያ ነጥብ መሰማት ጀምሯል። ይህን የሚሉቱ መሳሪያ ማንሳቱ ላይ እየሰሩ ለመሆናቸው ምንም ማረጋገጫ የማይገኝላቸው ጠበቅ ተደርገው ሲያዙ ደግሞ ዛሬም በትናንትናው ችናኔ ብቻ ለመኖር የሚቃጣቸው ራሳቸውንም ጓዶቻቸውንም በአጉል ተስፋ በመደለል የሚኖሩ ናቸው። ዋናው ጥያቄ ሕዝብና ሃገርን ከወያኔ ኢሕአዴግ ጭቆና ለማላቀቅ ማናቸውንም ተግባራዊ እንቅስቃሴ እናድርግ ነው። ለመሆኑ የኢሕአፓ የትግል ስልት ሁለ-ገብ መሆኑ በፕሮግራሙ ላይ ቁልጭ ብሎ ሰፍሮ የለ እንዴ? “የእርቅና የድርድር መንገድ ትናንት አልሰራም። ነገም አይሰራም” ለሚሉ ትናንት የተሞከረው ምስክር ነው እንበል ስለነገ እርግጠኛ ሆኖ ለትንቢት መቃጣት ተገቢ ነው? ይልቁንስ ትግሉን በሁሉም መስክ ማፋፋሙ አይሻልም? ይኸው የነቢይነት ባሕርይና ከዚህ ውጭ አማራጭ የለም የሚሉ አካሄድ ነውኮ ከመሰረታዊ ችግሮቻችን አንዱና ዋነኛው ሆኖ ሲጎዳን የኖረ። ሕዝቧም ወገናችን። ኢትዮጵያም የሁላችን። ሁላችንም ይበጃል የምንለውን ሳንደብቅ ባደባባይ መግለጹና ከተሳሳቱ በብዙሃን ድምጽ በመታረም በብዙሃን ውሳኔ የሚመራ ስርዓት ለመመስረት አይደለም እንዴ የሕዝባዊ ትግሉ አንዱ ዓላማ?

ውድ አቶ ታደለ!

ለመሆኑ ክንፈ አብርሃ በስብሰባው ላይ ተገኝቶ የትኛውን የማናውቀውን ቡራኬ ሰጠን? ጨፍጫፊዎች በሕዝባዊ ስብሰባ ላይ መገኘታቸው ሕዝባዊ ያደርጋቸዋል ብለን እንፈራ እንቸር ይሆን? ክንፈ በአለቆቹና በራሱም ትዕዛዝ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደረሰውንና እያደረሰ ያለውን እስር እንግልት ስደትና ሞት በውጭ ሃገር በተለይም በካናዳ መንግስት ተወካዮች ፊት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ልጆች በማስረጃ የተደገፈ የምስክርነት ቃል ቁጭ ብሎ ለመስማት ህሊናውን ሳይኮሰኩሰው እኛን ለምን ሊኮሰኩሰን ቃጣ? ለመሆኑ ዶክተር ጌታቸው ከሙያ ጋር በተያያዘ ምክንያት ብቻ

የስብሰባው ተጋባዥ እንግዳ ሆነው በክንፈ አብርሃ ጀሮ የግፍና የመከራ ገድሉን ሊያንቆረቁሩለት መቻላቸዉ የሚያስወቅሳቸው ነውን?

በመጀመሪያዉ ምእራፍዎ ላይ “ ዶክተሩ ወያኔ እስረኞችን ለቆ ለእርቅ አመች ሁኔታ ይፍጠር ሲሉ..” ብለዉ፣ ዝቅ ብለዉ በመደምደሚያዎት ላይ “...ሽንበቆ ምሰሶ ይሆን ይመስል ወያኔ ለእርቅና ለዴሞክራሲ ተዘጋጅቷል ብሎ ራስንም ሕዝብንም ማሳሳት ሃጤያት ነዉ።” ይላሉ። ለምን ያልተባለና ያልነበረን በማቅረብ ሕዝብን ሊያሳስቱ ይሞክራሉ? ኢሕአፓስ ስለታሰሩ አባላቱ ለአለም ህብረተሰብ የይፈቱ ጥያቄ ማቅረቡን ለምን እንደጥፋትና እንደወንጀል ያዩበታል? የነዚህን የኢሕአፓ አባላት ሂዎት ለምን ዝቅ አድርገዉ ለማየት ቃጣዎት? ቃሊቲ ያሉ መሪዎችስ እየተደራደሩ አይደሉም? መደራደራደር እራሱን ችሎ ጥፋት ነዉ ያለወት ማን ነዉ? እንደኔስ መደራደር ጥፋት አይደለም፤ ጥፋት የሚሆነዉ ተደራድሮ የሕዝብን ጥቅም አሳልፎ መሸጥ ነዉ። ዶክተሩ ደግሞ የሕዝብን ጥቅም አሳልፈን እንስጥ አላሉም። ልንደራደር የሚያስችን ሁኔታ ስለለለ ወያኔን ለማስገደድና ወደድርድር ለማምጣት የተባበረ ትግል እናድርግ ነዉ ያሉት። ይህም አግባብነት ያለዉ ነዉ። ትግሉ ለነጻነትና ለመኖር እንጂ ለመታገል ሲሉ ትግል አይደለም። ትግሉ ለመኖር ነዉ። መኖር ደግሞ ከተባለ በነጻነት ነዉ። ለሞሞት ግን ትግል የለም ለመኖር እንጂ። ድርድርም ለመኖርም ለነጻነትም ከሆነ ጥሩ ነዉ። ዶክተር ጌታቸው የወያኔ ተወካይ በተገኘበት አዳራሽ መገኘታቸው ‘ከወያኔ ወገኑ እንዴ?’ የሚል አንድምታ ያለው ጥያቄ ማስነሳቱ ግለሰቡን ራሱን ዝቅ አድርጎ ማየት አይሆንም? ትንሽ ሰው ትንሽ ነው፤ አንሶ ያሳንሳል- ይላል ያገራችን ሰው። ካንድ ወንዝ እንደተቀዳ ያንድ ሃገር ልጅ ልዩነቶቻችን እንዳሉ ሆነው ቢያንስ በመከባበር ብንኖር ምናለበት? አንዳችን አንዳችንን ለማዋረድና ለማሳነስ በደከምን ቁጥር እኮ እግረመንገዳችንን የተዋረደ ዜጋና ሃገር እየገነባን መሆኑ ሊታወሰን ይገባል።

የአምባገነኑን የመለስ መንግስት ባልደረቦችን ይሁን ጋሻጃግሬዎቹን በየትኛዉም መድረክ ማጋለጥና መቆሚያ መቀመጫ ማሳጣት የትግሉ አካል እኮ ነዉ። እድሉ ሲገኝ ፊት ለፊት፣ ግንባር ለግንባር፥ አይን ለአይን ገጥሞ በዓለም አቀፍ ተመልካቾች ፊት ማጋለጥ የሁለንተናዊዉ ትግል አካል የሆነዉ የዲፕሎማሲያዊዉ ትግል ትልቁ ክፍል እኮ ነዉ። ሌላ አማራጭና አቅሙ ካለ መልካም ነዉ። ተቀምጠ ምንም ሳያደርጉ፣ በሟርትና በውግዘት ብቻ የዲፕሎማሲያዊዉን ትግልና ጥረት በማጣጣል እኮ ድል አይገኝም። እርስዎም ድርድር አይሞከርም ከሚሉት ሲመደቡ መለስም ሊደራደር ፈቃደኛ አለመሆኑ ጠፍቶዎት አይመስለኝም፤ እንዲያዉ ለጉራዉ እንጂ። ወያኔን ለድርድር ለማምጣትም እኮ ትግልን ይጠይቃል።

ሌላው ሊታወቅ የሚገባው ጉዳይ ዶክተር ጌታቸው በግል የተጋበዙ በመሆኑ በግል በቀረቡበት መድረክ ሁሉ የግል ሃሳባቸውን መሰንዘር የሚችሉበት ሰብአዊ ነጻነታቸውን ማክበር ተገቢ ነው። የኢሕአፓ መሪዎች ድርጅታቸውን የሚመሩበት ደንብና ስርዓት ያላቸው በድርጅታቸው ውስጥ ባሉ ብዙሃን ጓዶቻቸው ውሳኔ የተሰጠባቸውን የጋራ መመሪያዎች የሚያከብሩ ለነዚህም ተግባራዊ መሆን የሚደክሙ እንጂ የቤተሰቦቻቸውን፣ የግል ጓደኞቻቸውን፣ የሌሎች የውጭ የሙያ ባልደረቦቻቸውን ወይም የግል አመለካከቶቻቸውን ሁሉ የሚያስተናግዱት በኢሕአፓ ፕሮግራም መሰረት፤ እንዲያው ለሁሉም ጉዳይ እንደጉንዳን ባንድ ስርጥ መንገድ ብቻ የሚነጉዱ አድርጎ ማየትም ስህተት ነው። የኢሕአፓን መሪዎች ከተወሰነላቸው  ውጭ የማያስቡ ወይም የማያደርጉ እግር ተወርች የታሰሩ አድርጎም እንደመመልከት ያስቆጥራል። እንደሌሎች አባላት ሁሉ የኢሕአፓም መሪዎች የግል ነጻነታቸው የተጠበቀ ነው። በግል በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት በግል በስብሰባዎች ተገኝተው የግል ሃሳባቸውን በሰጡ ላይ ሁሉ ከከፍተኛ የአመራር አካል ማስተባበያ የመስጠት ባህል ስለሌለና ስለማይገባም አቶ ታደለ ምክርዎ ተቀባይነት ይኖረዋል ለማለት ያዳግታል።

<u>አንድ እውነት ላስረግጥልዎ። ኢሕአፓ የተዋቀረበት መሰረት በቀላሉ የማይናጋ በውድ አባላቱ ክቡር የሕይወት መስዋእዕትነትና በቋሚዎቹም ንቁ ተሳትፎ የተማገረ ስለሆነ አንድነታችን ጥብቅ ነው።</u>

ልዩነቶቻችን ጌጦቻችን ናቸው። አናፍርባቸውም። የነጻነታችንና የድርጅታችን ዴሞክራሲያዊነት መገለጫዎችም ናቸው። አብረውን ይኖራሉ። ኢሕአፓም ለዘላለም ይኖራል- ያለጥርጥር።

በመጨረሻ እርስዎ "የምሁራን" ስላሉት ስለአኦታዋው ስብሰባ አንድ ሃቅ ላስጨብጥዎ። የሶሴፓ-ካናዳ አባላትና ደጋፊዎች ያዘጋጁት የሜይ 5 2007 ስብሰባ ለሌሎችም ተመሳሳይ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾ ድርጅቶች በአርአያነት ሊጠቀስ የሚችል ታላቅ ኢትዮጵያዊ አኩሪ ተግባር የተከናወነበት ነው። ሶሴፓ-ካናዳ እንዲህ ዓይነቱን ተግባር ሲፈጽም ይህ የመጀመሪያው ባይሆንም ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች፣ በስደተኞች፣ ለሃገራቸውና ለወገኖቻቸው ነጻነትና እኩልነት እውን መሆን ያላሰለሰ ትግል በማድረግ ላይ ስላሉ ኢትዮጵያውያን አፈ ሕዝብ ሆኖ ያገለገለና ዛሬም በማገልገል ላይ የሚገኝ ጠንካራ ድርጅት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ድርጅት ሊረዳና ሊበረታታ ይገባዋል። በርቱ ሶሴፓ-ካናዳዎች።

ለሁሉም ከመጠምጠም መማር ይቅደም!!! ሃገርና ሕዝብ የሚድነው በሰከነ አዕምሮ ማሰብ ሲቻል ብቻ ነው!!!

ሰላምና ጤና

ክብርና ምስጋና።